**ኢትዮ-ካናዳውያን ኔትዎርክ ለማህበራዊ ድጋፍ**

**ETHIO-CANADIAN NETWORK FOR ADVOCACY AND SUPPORT**

(204) 334-7040 Email: info@ecnas.ca Website: www.ecnas.ca twitter.com/ecnas.ca facebook.com/ecnas.ca


# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያንን ለመከፋፈል የተከፈተው ዘመቻ ባስቸኳይ ይቁም!

ከኢትዮ-ካናዳውያን ኔትዎርክ ለማህበራዊ ድጋፍ የተሰጠ የአቋም መግለጫ

ጥር 30፣ 2015 (February 7, 2023)

የኢትዮ-ካናዳውያን ኔትዎርክ ለማህበራዊ ድጋፍ (ኢክናስ) የፌደራል መንግሥት፣ የኦሮሚያ መንግሥት እና የፀጥታ ሃይሎች በመቀናጀት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ላይ እያካሄዱት ያለውን እና አገራችን ኢትዮጵያ ከ 2 ዓመታት አውዳሚ ጦርነት በኋላ ያገኘችውን አንፃራዊ ሠላም አደጋ ላይ የሚጥል ህገ-ወጥ ዘመቻ አጥብቆ ይቃወማል።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ለካቢኔ ሚኒስትሮቻቸው ያደረጉት ንግግር እና ማብራሪያ የተዋህዶ ዕምነት ተከታዮችን ብቻ ሳይሆን ለአገራቸው ሠላም እና ዕድገት የሚመኙ መላው ኢትዮጵያውያንን ያሳዘነ፣ አገራችንን ለከፍተኛ አደጋ የሚያጋልጥ እና በይዘቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘወትር በንግግራቸው የሚሰብኩትን አንድነት የሚያፈርስ ሆኖ አግኝተነዋል። በመሠረቱ “ሃይማኖት እና መንግሥት መቀላቀል የለባቸውም” የሚለውን መርህ እንቀበላለን። ነገር-ግን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግርም ሆነ በተግባር መሬት ላይ የሚታየው ሃቅ የሚያሳዩት መንግሥት በህገ-ወጥ እና የቤተ-ክርስቲያኗን መተዳደሪያ ቀኖና በጣሰ መንገድ ራሱን ሲኖዶስ አድርጎ የሾመውን ቡድን በግልፅ መደገፉን ነው። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን እንደማንኛውም የአገሪቱ ተቋሞች ህጋዊ ሰውነት ያላት፣ በራሷ ቀኖና እና ህጋዊ-ሲኖዶስ የምትመራ፣ አገልጋዮቿን የምትሾም እና ለአገግሎቷም የምታውለው ንብረት እንዳላት እየታወቀ መንግሥት ለማንኛውም ህጋዊ-ተቋም የሚያደርገውን ጥበቃ እና ህግ የማስከበር ሥራ ስለከለከላት ህገ-ወጡ ቡድን ቤተ-ክርስቲያናት እየሰበረ፣ ንብረት እየቀማ እና በሠላማዊ መንገድ “ቤተ-ክርስቲያናችን አትከፈልም” እያሉ በፀሎት እና በመዝሙር ድርጊቱን የሚቃወሙ ምዕምናንን በኦሮሚያ ፀጥታ ሃይሎች አጋዥነት እያስደበደበ፣ እያሳሰረ እና እያስገደለ ይገኛል። በዕምነቱ ተከታዮች የተከበሩ ጳጳሳት እና መምህራን ከሚያስተዳድሯቸው አገረ-ስብከቶች እየተባረሩ እና ወደ ደብሮቻቸው እንዳይደርሱ እየተደረጉ ይገኛሉ። ይህ በፍፁም የመንግሥትን “በሃይማኖት ጣልቃ አለመግባትን” ሳይሆን የሚያሳየው ግልፅ የሆነ የፖለቲካ አላማ ያለው ጣልቃ ገብነትን ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን የዕምነቷ አስተምሮ ምዕምናን በሚገባቸው ቋንቋ መሆን እንዳለበት እንደምታምን እና ይሄንን ሰማያዊ ግዴታዋን ለመወጣት በኦሮሚያም ሆነ በሌሎች ክልሎች እጅግ አበረታች የሆኑ ጥረቶችን ስታደርግ መቆየቷን አሳውቃለች። በዚህ ረገድ ቤተ-ክርስቲያኗ ብዙ ተጨማሪ ሥራ የሚጠበቅባት ቢሆንም ብዙ የኦሮምኛ ቋንቋን የሚናገሩ ጳጳሳትን ከመመደብ አንስቶ፣ የአካባቢውን ቋንቋ የሚናገሩ ወጣቶችን በማሰልጠን፣ የሰንበት ት/ቤቶችን በማስፋፋት፣ ማህበራትን በማቋቋም፣ ወጣቶችን ወደ ገዳማት በመላክ እና የቤተ-ክርስቲያኗን ሥርዐተ-ሃይማኖት በማስተማር እንዲሁም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ አስተምሮ በማስመረቅ በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ በአብዛኛው በታዎች ቅዳሴ፣ ሰበካ እና ዝማሬ በኦሮምኛ እንዲካሄዱ ማድረግ አስችላለች። ይህንን ሥራም በበለጠ ለማስፋፋት ሲኖዶሱ በሥሩ ልዩ መምሪያ አደራጅቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የቤተ-ክርስቲያኗ መሪዎች በአደባባይ አሳውቀዋል። ስለዚህ በህገ-ወጡ ቡድን በኩል ያለው ጥያቄ የቋንቋ ቢሆን ኖሮ የተጀመረው ሥራ እንዲስፋፋ በህጋዊ መንገድ ግፊቱን ማድረግ ይችል ነበር። በግልፅ የሚታየው የቡድኑ ተልዕኮ ግን በአገሪቱ የተተከለው ከፋፋይ የብሄር ፖለቲካ እና አወቃቀር በቤተ-ክርስቲያኗም እንዲተገበር ማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን በተለይ ባለፉት 30 እና 40 ዓመታት ከፍተኛ የሆነ መዋከብ፣ የቤተ-ክርስቲያናት መቃጠል፣ የአባቶች መሰደድ፣ የምዕምናን ድብደባ እና እሥር ሁሉ ያስተናገደች ናት። በለውጡ ማግሥት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰላም እና ለአንድነት ባለው ጥማት የለውጡን ሃይል አቅፎ እና ደግፎ የቆየ ቢሆንም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ግን ሰላም እየጠፋ እና የዜጎች በህይወት የመኖር መብት ሁሉ እየተጣሰ፤ ህዝብም ጩኸቱን የሚሰማው መንግሥት አጥቶ ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቋል። በለውጡ ማግሥት የታየው የተሥፋ ጭላንጭል እንደ ጉም እየበነነባቸው ካሉት የአገራችን ተቋማት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን አንዷ ነች።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት፣ የኦሮሚያ መንግሥት እንዲሁም የብልፅግና ፓርቲ መገንዘብ ያለባቸውጉዳይ በቤተ-ክርስቲያኗ ላይ ያነጣጠረው ፖለቲካዊ ጫና አገሪቱን የሚከፋፍል፣ በሃይማኖቶች እና በብሄሮች መሃል ፀብ እና ጥርጣሬ እንዲፈጠር ለሚፈልጉ ሃይሎች በር የሚከፍት፣ የንፁሃንን ህይወት የሚቀጥፍ፣ ንብረት የሚያወድም እና የኢትዮጵያ ህዝብ በለውጡ ላይ የነበረውን የተስፋ ጭላንጭል ጨርሶ የሚያጠፋ መሆኑን ነው።

ስለዚህም ኢክናስ መንግሥት እና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ያሳስባል፡

1. ከህግ-ውጭ እራሱን ሲኖዶስ ብሎ የሰየመው ቡድን በጉልበት የያዛቸውን ቤተ-ክርስቲያናት እና ንብረት ለቆ እንዲወጣ፤
2. የፌደራልም ሆነ የኦሮሚያ ክልል ፀጥታ ሃይሎች ሰላማዊ ፀሎት እና ዝማሬ በሚያሰሙ ንፁሃን ዜጎች ላይ እየፈፀሙ ያለውን እሥር፣ድብደባ፣ ግድያ እና ወከባ እንዲያቆሙ፤ ህይወት እንዲጠፋ ያደረጉ የፀጥታ ሃይል አባላትም በህግ እንዲጠየቁ፤
3. በህጋዊ መንገድ በፓትርያርኩ (በቅዱስ ሲኖዶስ) የተሾሙ የአገረ-ሥብከቶች ጳጳሳት እና አስተዳዳሪዎች ወደየደብሮቻቸው ሄደው ከምዕምናን ጋር እንዲገናኙ እና መደበኛ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው፤
4. የቤተ-ክርስቲያኗ ህጋዊ ሲኖዶስ በሰጠው መግለጫ የተወገዘው ሲኖዶስ አባላት ይቅርታ ጠይቀው ወደ እናት ቤተ-ክርስቲያናቸው መመለስ እንደሚችሉ በር የከፈተ ስለሆነ፣ የአገር ሽማግሌዎች ይህ ከዳር እንዲደርስ እና ችግሩ በቤተ-ክርስቲያኗ ቀኖና መሠረት እንዲፈታ እና ሠላም እንዲወርድ ጥረት እንዲያደርጉ፤
5. የፌዴራሉም ሆነ የክልሉ መንግሥት በኢ ፌ ድ ሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 11 (ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 3) በሚደነግገው መሰረት በሀይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ መግባቱን እንዲያቆም፤
6. ከላይ የተጠቀሱትን በሟሟላት መንግሥት ሃላፊነቱን ካልተወጣ በህይውትም ሆነ በንብረት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ ተጠያቂ እንደሚሆን እናሳስባለን::

ሠላም፣ አንድነት፣ ፍቅር ለኢትዮጵያ!

የኢትዮ-ካናዳውያን ኔትወርክ ለማህበራዊ ድጋፍ (ኢክናስ)